
**ይድረስ ለኢትዮጵያዊያን**

የከበረ ሰላምታዬ ከናሚቢያ ዋና ከተማ (ዊንድሆክ) ይድረሳችሁ እያልኩ ስለምወዳት እና ስለምኖርባት ሀገር ስለናሚቢያ በጣም በትንሹ አሳጥሬ ላወጋችሁ ወደድሁ ።

ናሚቢያ በደቡባዊ ምእራብ አፍሪካ የምትገኝ ሀገር ናት። በጀርመን ቀጥሎም በደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ቅኝ ትገዛ ነበር ። በደቡብ አፍሪካ ኣፓርታይድ ቅኝ ግዛት በነበረችበት ጊዜ ይገኟት የነበሩት የአፓርታይድ ፍልስፍና አራማጆች ህዝቡን በቀለም በቋንቋ በብሔረሰብ እና በዘር ከፋፍለዉ እያንዳንዱ ብሔረሰብ በሀገሪቱ ላይ የራሱ የሆነ ክልል እንዲኖረው አድርገው ነበር።

ከዚህ በታች ባለው ካርታ ላይ እንደምትመለከቱት ወደ አሥር የብሔረሰብ ክልሎች ተፈጥረው ነበር። የክልሎቹ ስያሜም ከብሔረሰቡ ስም ጋር አንድ አይነት ነበር። ለምሳሌ የኦቫምቦ ብሔረሰብ ክልል ኦቫምቦላንድ ፣ የዳማራ ብሔረሰብ ክልል ዳማራላንድ እያለ በካርታው ላይ እንደምታዩት ይቀጥላል።




Odendaal Commission 1964

ኤቶሻ ለዱር አራዊቶች የተከለለ ፓርክ ነው። ዊንድሆክ ያለችበት መሃል መሃሉ የሀገሪቱ ክፍል ደግሞ ነጮቹ የሚቆጣጠሩት እና ዋና ዋና ከተሞችን ያካተተ ሆኖ የነጭ ገበሬወች የያዙት ሰፋፊ እርሻወች ያሉበት ነበር።

የብሔረሰብ ክልል አወቃቀሩ ሀገር አቀፍ ብቻ ሳይሆን ዋና ዋና ከተሞችም በብሔር እንዲዋቀሩ ተደርገው ነበር። መጀመሪያ ከተማው የነጭ፣ የክልስ እና የጥቁር ተብሎ ለሶስት ከተከፈለ በኋላ የጥቁሮቹ ክፍለ ከተማ ወረዳዎች ለየብሔረሰቡ ተከፋፍለው እያንዳንዱ ብሔረሰብ በየከተማው የመኖሪያ ሰፈር ክልል ነበረው። ለምሳሌ በዋና ከተማዋ በዊንድሆክ ዳማራ ሎኬሽን የሚባለው ዳማራ ብሔረሰብ የሚኖርበት ክፍለ ከተማ (ሰፈር) ሲሆን ኦቫምቦ ሎኬሽን ደግሞ የኦቫምቦ ብሔረሰብ ሰፈር ማለት ነው። ኮማስዳል የክልሶች ሰፈር ፤ ዋናሄዳ ደግሞ ለድብልቆች የተወሰነ ሰፈር ወዘተ እያለ ይቀጥላል። እንደዛ እያለ እያንዳንዱ ክፍለ ከተማ በብሔረሰብ እና በዘር ላይ የተመሰረተ ነበር። ሰፈሮቹም እስከ አሁን ድረስ አሉ። ይህም አዲስ አበባን የትግሬ ክፍለ ከተማ፣ የኦሮሞ ክፍለ ከተማ፣ የአማራ ክፍለ ከተማ ወ ዘ ተ ብሎ እንደመከፋፈል ማለት ነው።

በዚያን ዘመን የሰው ልጆች እንደዛሬዋ ኢትዮጵያ ብሔር፣ብሔርሰብ እና ህዝቦች ሳይሆን ነጮች ጥቁሮች እና ክልሶች በማለት ነበር መንግስት የሚፈርጃቸው። የዚህ አይነቱ ኣስተዳደር ባንቱስታን በመባል ይታወቃል። በወቅቱ ሃገሪቱን ይገዛ የነበረው የአፓርታይድ መንግስት እንደሚለው እንደዚህ መክለሉ 'እያንዳንዱ ብሔረሰብ ወይም ዘር እራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር እና ያለማንም ተጽዕኖ ባህል እና ቋንቋውን እንዲያሳድግ' ነበር። በቋንቋ ፣ በዘር ፣ በሃይማኖት ወይም በብሔር ላይ ተመስርቶ የተፈጠረ የአፍሪካ ሀገር አለመኖሩ እየታወቀ እነዚህ የአፓርታይድ ቅኝ ገዥወች ግን ደቡብ አፍሪካን እንዳደረጓት ሁሉ ናሚቢያንም በዘር በቋንቋ እና በብሔረሰብ ከፋፍለው ይገዟት ነበር።

ማንኛውም ሰው ከክልሉ ሲወጣ የይለፍ ወረቀት አለበለዚያም መታወቂያ ካርዱን መያዝ ያስፈልገው ነበር። መታወቂያ ካርዱ ላይ ብሔረሰቡ ስለሚጻፍ ያለ ፍቃድ ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው መሄድ ክልክል ነበር። የጥቁሩ ህዝብ የተለያዩ ብሔረሰቦች የሚገናኙት በነጮቹ ስር ሲሰሩ ብቻ ነበር። ከስራ ሰዓት በኋላ ሁሉም ወደ ተመደበለት ሰፍር ሄዶ ከራሱ ብሔር ሰወች ጋር ብቻ ይኖር ነበር። በወቅቱ የነበረው መንግስት ኢንደሚለው ቁጥጥሩ ህዝቡን ከወንጀለኞች እና ከሽብርተኞች ለመጠበቅ ነበር። ፈረንጅ እና አፍሪካዊም የፍቅር ግኑኝነት ከፈጠሩ ወንጀል ነበር።

በዚህ ወቅት የነበረው የአፓርታይድ መንግስት እራሱን ልማታዊ መንግስት ብሎ ባይጠራም ከፍተኛ የሆነ የልማት እንቅስቃሴ ያደርግ ነበር። የመኖሪያ ቤቶችን መንገዶችን የባቡር ሃዲዶችን እና ሌሎችንም ነገሮች በብዛት ይሰራ ነበር፤ እነዚህ መሰረተ ልማቶች ናሚቢያን እስከ አሁን ድረስ እያገለገሏት ይገኛሉ። በዚያን ወቅት የህዝቡ ኑሮም ነጻነት የሌለው

ይሁን እንጂ መሰረታዊ ፍላጎቶቹ የተሟሉ ነበሩ። የከተማ ልማት እየተባለ ጥቁሩ ህዝብ ከሚኖርበት ቅዬው በግድ እየተፈናቀለ ወደ ከተማ ዳር ኮንደሚኒየም ሳይሆን ቤት እየተሰራለት ይሰፍር ነበር። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ካቱቱራ የሚባለው በ1961 የተመሰረተው የዊንድሆክ ክፍለ ከተማ ነው። “ካቱቱራ” ማለት በሄሬሮ ቋንቋ ሰወች መኖር የማይፈልጉበት ቦታ ማለት ነው። ካቱቱራ ደግሞ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በብሔረሰብ ወረዳወች የተከፋፈለ ነው። የወቅቱ መንግስት ለራሱ ህልውና ሲል በብሔረሰብ የከፋፈለው ህዝብ ላይ ጠንካራ የፖሊስ እና የስለላ ሃይል አሰማርቶ ይቆጣጠር ስለነበር ተራ ወንጀል ኣይበዛም ነበር። በዚህም ምክንያት ስርዓቱን የተቃወሙ ልማት እና ሰላም የማይፈልጉ ኣሸባሪወች እየተባሉ ድብደባ እስራት እና ስደት ይደርስባቸው ነበር።

በዚያን ዘመን በኢትዮጵያ እና በሌሎች ነጻ በወጡ የአፍሪካ ሀገሮች ይደርስ የነበረዉን የጦርነት እና የረሃብ ሰቆቃን እንደምሳሌ በመጠቀምም ከፋፋዩ የአፓርታይድ መንግስት የናሚቢያን እና የደቡብ አፍሪካ ህዝቦችን ነጻነት ብላችሁ እንደነሱ በረሃብ እና በጦርነት እንዳታልቁ እያለ ያስፈራራና ያስጠነቅቅ ነበር። የዚህ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ የሆነው ህዝብም ኢትዮጵያን ከሆነችው በላይ ደሃ አድርጎ እስከ አሁን ሲገምት ይስተዋላል።

ሆኖም ገና ከጅምሩ የናሚቢያ ብሔር-ብሔረሰቦች በወቅቱ የነበረው የአፓርታይድ መንግስት ከፋፋይ ስርዓት ሊዋጥላቸው ስላልቻለ፤ ኣላማውም እነሩስን ከፋፍሎ መግዛት መሆኑን ሁሉም ስለተረዱ፤ በሚስጥር ህብረት በመፍጠር ግዙፉን ዘረኛ አፓርታይድ የነጮች መንግስት ሊያስወግዱት ቆርጠው ሲነሱ፤ የጥቁር ህዝቦች ኩራት የነበረችው ኢትዮጵያ ለብዙ የአፍሪካ ሀገሮች እንዳደረገችው ለናሚቢያም ነጻነት ብዙ እረድታለች።




የናሚቢያን የነጻነት ጥያቄ በመደገፍ ከናሚቢያ የነጻነት ታጋዮች ጋር በመሰለፍ ኢትዮጵያ አና ላይቤርያ ዘረኛውን የደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ መንግስት በአለም ፍርድ ቤት ከሰውት ስለ ናሚቢያ ነጻነት ተሟግተዋል። ፍርድ ቤቱ ግን መጨረሻ ላይ እናንተ ስለ ናሚቢያ አያገባችሁም ብሎ ስለፈረደ የናሚቢያ የነጻነት ታጋዮች ወደ ትጥቅ ትግል ገቡ።

በዚህም ትጥቅ ትግል ኢትዮጵያ የናሚቢያን ነጻ አውጪወች አቅሟ በፈቀደው ሁሉ በኀይለሥላሴ አና በመንግስቱ ጊዜ እረድታለች። በብሔረሰብ እና በዘር እንዲከፋፈሉ የተደረጉት ናሚቢያውያንም እኛ ሁላችን በሰዉነታችን አንድ ነን ብለው በድብቅ እየተገናኙ አንድነታቸውን አጠናክረው ከፋፋዩን ስርዓት በቃህ ብለው ሊፋለሙት ሲነሱ ሌሎችም ሀገሮች ደግፈዋቸው ከብዙ ትግል በኋላ በተባበሩት መንግስታት ተሳትፎ የናሚቢያ ነጻነት በምርጫ ማርች 20, 1990 እዉን ሆነ። የሀገሪቱ መንግስት አርማም **አንድነት ነጻነት** እና **ፍትህ** ላይ የተመሰረተች ሀገር መሆኗን ያረጋግጣል።

በነጻነቱ ዋዜማ የተዘጋጀው የሀገሪቱ ህገ መንግሥት እያንዳንዱን ግለሰብ የሰው ልጅ በመሆኑ ብቻ በነጻነት በፍትህ በሰላም ደስ ብሎት ምንም አይነት መድሎ ወይም ልዩነት ሳይደረግበት በፈለገው የሃገሪቱ ክፍል ሄዶ የመኖር መብቶች ያረጋገጠ ነው። የናሚቢያ ህገ መንግስት የመጀመሪያ ፫ አረፍተ ነገሮች እነዚህ ናቸው። ሙሉውን ኢንተርኔት ላይ ታገኙታላችሁ።

**Whereas** recognition of the inherent dignity and of the equal and inalienable rights of all members of the human family is indispensable for freedom, justice and peace;

**Whereas** the said rights include the right of the individual to life, liberty and the pursuit of happiness, regardless of race, colour, ethnic origin, sex, religion, creed or social or economic status;

**Whereas** the said rights are most effectively maintained and protected in a democratic society, where the government is responsible to freely elected representatives of the people, operating under a sovereign constitution and a free and independent judiciary;



የመጀመሪያው የናሚቢያ የነጻነት ትግል መሪ ዶክተር ሳም ኑዮማ ህይወታቸውን በሙሉ ለናሚቢያ ነጻነት እና ለአፓርታይድ ሥርዐት መወገድ እንደ ኔልሰን ማንዴላ የታገሉ ቆራጥ መሪ ናቸው። ከነጻነት በኋላ የመጀመሪያው የናሚቢያ መስራች ዲሞክራሲያዊ ፕሬዝዳንት በመሆን በህገ መንግስቱ አስከተፈቀደላቸው ግዜ ድረስ አገልግለው በሰላም እና በፍቃደኝነት ከስልጣን በመውረድ አርዓያነት ያለው ተግባር ፈጽመዋል። በስልጣን ዘመናቸው ሰላም እና እርቅ፣ የሰው ልጆች ሁሉ እኩልነት እና ነጻነት ፣ ፍትህ እና ዲሞክራሲን መሰረት አስይዘዋል።

በፎቶው ላይ ከማንዴላ ጋር ተያይዘው የሚታዩት ኑዮማ ዘወትር ለህዝባቸው የሚያሳስቡት ነገር ቢኖር አንድነቱን እንዲጠብቅ እና ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የጋራ ጥቅም እንዲጥር ነው። *"Remember, a united people, striving to achieve a common good for all members of society, shall always emerge victorious." Sam Nujoma.*



ኑዮማ እና በጥንት ጊዜ የመሰረቱት ፓርቲያቸው ስዋፖ (SWAPO) በሰው ልጆች ሁሉ አንድነት የሚያምኑ፤ ዘረኝነትን አጥብቀው የሚቃወሙ እና የተዋጉ፤ ጎሰኝነትን እና ብሔርተኝነት የማይፈልጉ፤ የሰዉን ልጅ በሰዉነቱ ብቻ የሚመለከቱ ናቸው።

ስዋፖ ፓርቲ የራሱ የሆነ መተዳደሪያ ህግ ያለው በዉስጡም ዲሞክራሲያዊ የሆነ የአባላት ውድድር በማካሄድ መሪወቹን የሚመርጥ ድርጅት ነው። ለገዥው ፓርቲ ለስዋፖ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ያላት ናሚቢያ “አንድ ሀገር አንድ ህዝብ” ነች ። ይህም መፈክር የጀግኖቹን ሀገር ናሚቢያን ከዳር እስከ ዳር ያስማማል። ካለፈው ተመክሮ በመነሳት የብሔር ክፍፍሉን ዘመን የሚመኝ ናሚቢያዊ የለም።

ኑዮማ ለናሚቢያ አንድነት ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም አንድነት ትልቅ ራዕይ ያላቸው መሪ ናቸው። በስልጣን በነበሩበት ወቅት አንድ ጊዜ ንግግር ሲያደርጉ ወደሚወዱት የሃገራቸው ባንዲራ እየጠቆሙ “አንድ ቀን አፍርካ አንድ ስትሆን ይሄ ባንዲራችን ሙዝየም ገብቶ የአፍሪካ ባንዲራ ብቻ ይውለበለባል” ነበር ያሉት።

ኢትዮጵያ የጥቁር ህዝቦች የነጻነት ፋና እንደመሆንዋ መጠን ብዙ የአፍሪካ ሀገሮች ባንዲራቸውን አረንጓዴ ቢጫ ና ቀይ እንዲኖረው ማድረጋቸው ይታወቃል። አድዋ ላይ ጀግኖቹ ኢትዮጵያዊያን የጣልያንን ጦር ደምስሰው ያውለበለቡት ባንዲራ ኢትዮጵያ ዉስጥ ተከልክሎ ሌሎች አዳዲስ የክልል ባንዲራወች ተፈጥረው ከዋናው ከባለ ኮከቡ ባንዲራ ጋር ይሰቀላሉ።

ናሚቢያ ደግሞ የክልል ባንዲራ ብሎ ነገር የለም፤ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የራሷን ባለ ጸሃዩን የናሚቢያ ባንዲራ እና የአፍሪካ አንድነት ባንዲራን አብራ ትሰቅላለች። የናሚቢያ ሰንደቅ ዓላማ ከአፍሪካ ባንዲራ ተለይቶ በአደባባይ አይሰቀልም። የናሚቢያ ብሔራዊ መዝሙርም ከአፍሪካ አንድነት ምዝሙር ጋር አብሮ ነው እንጂ ብቻውን አይዘመርም። ለናሚቢያ የአፍሪካ ቀን (May 25) የህዝብ በዓል ነው። ኢትዮጵያ ዉስጥ ያው የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ስለሆነች ታስቦ ይውል ይሆናል እንጂ እንደ ብሔረሰቦች እና የባንዲራ ቀን አይካበድም፤ አይከበርም።

ናሚቢያ ሰፋ ያለ አመለካከት ያላት አፍሪካ ተኮር እንጂ ብሔር ተኮር ሀገር አይደለችም። ሌላ ከተማ ላላየ የራሱ መንደር የዓለም ትልቋ ከተማ ትመስለዋለች ወይም ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል እንደተባለው በብሔር መመጻደቅ ምንጭን ወይም መንደርን የማድነቅ ያህል ነው ለናሚቢያዊያን።

ከላይ ከህገ መንግስቱ እንደጠቀስኩት የናሚቢያ ትኩረት የእያንዳንዱ ሰው መብት መከበር ላይ ነው። ይህም በመሆኑ እያንዳንዱ ግለሰብ (እኔ ከኢትዮጵያ የመጣሁትን ጨምሮ) ሰብአዊ መብቱ የተጠበቀ ነው። ባህሌ ነው ብዬ የፈለኩትን ብበላ እና ብጠጣ፣ የፈለግሁትን ልብስ ለብሼ እንዳሻኝ ስጨፍር ብውል፤ ወይም ባሻኝ ቋንቋ ብናገር እና ብጽፍ፤ የኔ የራሴ እንጂ የማንም ጉዳይ አይደለም።

ባለፈው ጊዜ ዕንቁጣጣሽን ኢትዮጵያዊያን ተሰብስበን አከበርን።ሌላውም ብሔረሰብ ወይም የዉጪ ዜጋ እንደዛ የማድረግ መብት አለው። እንደማንኛውም የሰለጠነ ሀገር ሁሉ ነገር በነጻነት እና በሰላም ነው እንጂ በግድ አይደለም።

የናሚቢያ ህዝቦች ክልል እንዲበጅባቸው አይፈቅዱም ፤ በአዲስ አበባዎች አባባል “ክልል ናሚቢያ ላይ ድሮ የተበላ እቁብ ነው”። በአሁኑ ጊዜ ናሚቢያ ያላት የአስተዳደር ክፍለ ሃገሮች ናቸው እንጂ የብሔረሰብ ክልሎች አይደሉም። በናሚቢያ የሰውን ብሔረሰብ መታወቂያ ላይ መጻፍ ከአፓርታይድ ስርዐት ጋር ሞቶ ተቀብሯል።

ማንኛውም ናሚቢያዊ በፈለገበት የሃገሪቱ ክፍለ ሃገር ሄዶ ኑሮ የመመስረት መብት አለው። መሬትም የግል ስለሆነ ሻጭ እና ገዢ ተስማምተው የሚጨርሱት እንጂ መንግስት ከደሃው በትንሽ ገንዘብ ነጥቆ ለሃብታም በጣም አትርፎ የሚሸጥበትና ትርፉን ወደ ኪሱ የሚያደርግበት ሁኔታ የለም። እንዳውም የአሁኑ የናሚቢያ መንግስት ትልልቅ እርሻወችን ከሃብታም ነጭ ገበሬዎች እየገዛ ለደሃው ሲያካፍል ነው የሚታየው።

ናሚቢያ ነጻ ወጥታ ስዋፖ የተባለው ፓርቲ የህዝቡ አመኔታ ባልተለየው እና አለም አቀፍ መስፈርቶችን በሚያሟሉ ዲሞክራሲያዊ ምርጫዎች እያሸነፈ ህዝቡን አንድ አድርጎ ከ ፪፮ አመት በላይ እየመራ ይገኛል። በዚህ ጊዜ ዉስጥ አንድም ጋዜጠኛ ታስሮ አያውቅም። የሃገሪቱም መንግሥት ሥልጣን ላይ ከመጣ ጊዜ ጀምሮ በፖለቲካ ግጭት ሰው እንኳን ሊያስርና ሊገድል ደብድቦም አያውቅም። የናሚቢያ ፖሊስ እና ጦር ሰራዊት በፖለቲካ ጉዳዮች ዉስጥ ጣልቃ አይገቡም። ፍርድቤቶች ነጻ ናቸው። ህዝቡ ሃሳቡን ያለ ምንም ፍርሃት ይገልጻል። የሀገሪቱ ባለ ስልጣኖች ለህዝብ በጣም ቅርብ ናቸው። ከፕሬዝዳንቶች ጀምሮ ሁሉም ከህዝብ ጋር መደባለቅን አይፈሩም። እስከ አሁን ፫ ፕሬዝዳንቶች ሥልጣን በሰላማዊ መንገድ ተለዋውጠዋል። ሁለተኛው ፕሬዝዳንት ፖሃምባ ያለፈው ዓመት የሞ ኢብራሂም ሽልማት ማሸነፋቸው ይታወሳል።

ወገኖቼ ይህን ያህል ስለምኖርባት ሀገር ናሚቢያ ካጫወትኳችሁ ይበቃል። ሀገራችን ኢትዮጵያ ከናሚቢያ በብዙ ነገር የተሻለች እንጂ የምታንስ መሆን የለባትም። ዘጠና ሚሊየን ጭንቅላት ያላትን ሀገር ሁለት ሚልየን ብቻ ካላት ጋር ማወዳደር አልፈልግም። ኢትዮጵያ ታላቅነቷን አውቃ እንደ ታላቅ ሀገር የሚያስቡ መሪዎች ሊኖራት ይገባል ባይ ነኝ።

ለአፍሪካውያን ጥሩ የነጻነት ምሳሌ ነበርን፤ በብሔር ፖለቲካ ተሞኝተን እራሳችንን በማዋረድ መጥፎ ምሳሌ አንሁን። በዚህ ወር ብቻ በብሔር ፖለቲካ ሰበብ ወገኖቻችን መሞታቸው ያሳዝናል! ያሳፍራልም! ናሚቢያ ከዚህ አይነት ችግር ነጻ ነች። አስተሳሰባችን ወደ ሀገር ብሎም አህጉር እና ዓለም ዓቀፍ ደረጃወች ማደግ እንጂ ወደ ታች መዝቀጥ የለበትም።

መልካሙን ሁሉ ለኢትዮጵያ ፣ ለናሚቢያ እና ለመላው የፍሪካ ህዝቦች ተመኘሁ። ቸር ይግጠምን።

አንድነት ተስፋዬ 16/01/2016

ዊንድሆክ

ናሚቢያ

Email: 100percentunity@gmail.com